የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 251702

ቀን ፡- ሐምሌ 26 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች-** እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካቾች ፡-** 1. አቶ ቢንያም ታመነ

2. አቶ ሔኖክ ታመነ

3. አቶ ቤዛነህ ታመነ

4. አቶ ያሬድ ታመነ

ቀረቡ- 2ኛአመልካች ስለሌሎች ወኪል ሆነው ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ ቆንጂት ኑሩ - ጠበቃ ዘላለም ብርሃኑ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ማጣራት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች ከሳሽ፣ ከ2ኛ-4ኛ ድረስ ያሉት አመልካቾች 2ኛ ጣልቃ-ገብ፣ ተጠሪ 1ኛ ጣልቃ-ገብ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርዶች አረጋጋጫ ለማድረግ አይገለግልም!

1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ግንቦት 25/2013 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ወላጅ አባታቸው ሟች አቶ ታመነ መኮንን መጋቢት 06/2013 ዓ/ም ከዚህ ዓም በሞት የተለዩ በመሆኑና ወራሽነታቸውን ያረጋገጡ መሆኑን በመግለጽ ውርስ እንዲጣራላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከ2ኛ-4ኛ ድረስ ያሉት አመልካቾች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት የሟች አባታቸን የውረስ ሀብት መጣራት ሂደት ልንሳተፍ ይገባል፣ ክርክር ያስነሳው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 1882 የሆነው ቤት አባታችን ከሟች እናታችን ወ/ሮ ታሪኳ ተገኝ ጋር በጋራ ያፈሩት ስለሆነ የእናታችን ድርሻም የመውረስ መብት አለን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ከሟች አቶ ታመነ መኮንን ጋር ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት በሚቆጠር ግንኙነት አብረን ቆይተን በ2006 ዓ/ም በተደረገ የባሕላዊ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ትዳር መስርተን ስንኖር በ2005 ዓ/ም ቀደም ሲል የነበረውን ቤት አፍረስን በአዲስ መልክ ሰርተነዋል፣ ተጨማሪ ክፍሎችንም ገንብተናል፣ ንብረቱ የጋራ በመሆኑ የሚስትነት ድረሻዬ ሊከበር ይገባል ብለዋል፡፡ 1ኛ አመልካች በተጠሪ ለቀረበው ማመልከቻ ባቀረቡት መልስ ተጠሪ የሟች አባታችን ሚስት አይደሉም፣ የሚስትነት ማስረጃው ሊስተባበል የሚችል ተራ ማስረጃ ነው፣ የባሕላዊ የጋብቻ ውል ሰነድ በሚል የቀረበው በሟች ያልተፈረመ ሀሰተኛ ሠነድ ነው ብለዋል፡፡ ከ2ኛ-4ኛ ድረስ ያሉት አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ ሚስት አይደሉም፣ የጋብቻ ውል ተብሎ የቀረበው ሀሰተኛ ነው፤ ፊርማ ምርመራ ይደረግልን፣ ንብረቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ እድሳት አልተደረገም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቱም ውርስ አጣሪ በመሾም ሪፖርት እንዲቀርብ ካደረገ በኂላ የግራቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ተጠሪ ሟች አቶ ታመነ መኮንን ሚስት ናቸው ወይስ አይደሉም በሚለው ጭብጥ ላይ የሰው ማስረጃ በመስማት ተጠሪ ከሟች አቶ ታመነ ጋር ከ2001 ዓ/ም  እስከ ጥቅምት 05 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት የሚቆጠር ግንኙነት መስርተው  ሲኖር የነበረ መሆኑ እና በኂም ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ/ም በባሕላዊ ጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ትዳር መስርተው ሲኖሩ የነበረ ስለመሆኑ በቀረበው የሠው ማስረጃ እና በ06/02/2006 ዓ/ም በተጻፈው የጋብቻ ውል ተረጋግጧል፣ ንብረቱን በ2005 ዓ/ም መሠራዊ ለውጥ የተደረገበት በመሆኑና በጋብቻ ውልም ተጠሪ የንብረቱ ተጋሪ ሆነው ውል ያደረጉ ስለሆነ ከ2ኛ-4ኛ ድረስ ያሉት አመልካቾች እናት ሟች ወ/ሮ ታሪኳ ተገኝ በንብረቱ ላይ ድርሻ የላቸውም፤ የንብረቱ ግማሽ ድርሻ የተጠሪ ሲሆን ቀሪው ግማሽ ድርሻ የሟች አቶ ታመነ መኮንን ወራሾች የሚከፋፈሉት የውርስ ድርሻ ነው ሲል የውርስ ሪፖርቱን በማሻሻል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ይግባኝ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ይሕ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካቾችም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሐምሌ 28/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ተጠሪ ከሟች አባታቻን ጋር ተደረገ በሚል የቀረበው የጋብቻ ውል የሟች ፊርማ አይደለም፣ ፊርማው ሊመረመር ይገባል በሚል ተከራክረን እያለ በፍ/ሕ/ቁ. 2008

መሠረት ፊርማው ሳይመረመር ወወሰኑ ስህተት ያለበት ነው፤ ክርክር ያስነሳው ንብረት ተጠሪ መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ አላደሱም፣ ስለመለወጡም በምትክ ዳኛ አልተረጋገጠም የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባል በማለት ለዚህ ችሎት የመራው ሲሆን ይህ ችሎትም አመልካቾች ተጠሪ በማስረጃነት ባቀረቡት የጋብቻ ውል ያለው ፊርማ የሟች አባታቸው አለመሆኑን ጠቅሰው ፊርማው በሳይንሳዊ የምርመራ ዘዴ እንዲመረመርላቸው ያቀረቡት መከራከሪያ ታልፎ ተጠሪ የሟች ሚስት ናቸው በሚል ግማሽ የሚስትነት ድርሻ እንዲካፈሉ መወሰኑ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት አዟል፡፡

ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ሰኔ 06/2016 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካቾች በማስረጃ ዝርዝር ጠቅሰው ፊርማ እንዲመረመር አልጠየቁም፣ ባቀረቡት ክርክር የፊርማ ምርምራ ይደረግ ስላሉ ብቻ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ የተጠቀሱ ማስረጃዎችን የማስቀረብ ኃላፊነት የለባቸውም፣ በቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ሚስት መሆናቸው ስለተረጋገጠ ተጨማሪ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ የማዘዝ ግድታ የለበትም፣ ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመስረቱ በቀረበው የሰውና የጽሁፍ የጋብቻ ማስረጃ ተረጋግጧል፣ በውሉ እማኞች የነበሩ ቀርበው ስለውሉ ትክክለኛነት መስክረዋል፣ የባለሙያ ፊርማ ምርመራና ውጤቱም እንደመጨረሻ ማስረጃ የሚወሰድ አይደለም፤ የተሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ የሚገባው ባለመሆኑ እንዲጸናልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም ሰኔ 24/2016 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በዚህ ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ የውርስ ሀብት ይጣራልን በሚል የቀረበ ዳኝነት ክርክሩ የተጀመረ ሲሆን ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ-ገብነት ማመልከቻ ከሟች አቶ ታመነ መኮንን ጋር ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ/ም በባሕላዊ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ጋብቻ የፈጸሙና ጋብቻ ውል ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 1882 የሆነው ቤት ግማሽ ድርሻ ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በጋብቻ ውል ላይ ያለው ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ፊርማውን በፎረንሲክ ምርምራ ሳያደርግ ምስክሮችን በመስማት ተጠሪ ከሟች ጋር የጋብቻ ውል አላቸው፣ ንብረቱንም በውል የጋራ አድርገውታል በማለት የተጠሪን ግማሽ ድርሻ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ

ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ አጣርቶ በመወሰን የተከራካሪዎች የመደመጥ መብት ማክበርና የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን እውነት የመፈለግ ዓላማ የማሳካት ኃላፊነት አለበት። ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ፣ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ፍርድ ቤቱ ሕጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል። ክርክሩን በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰንም ፍርድ ቤት በሕግ የተጣለበትን ክርክርን የመምራት ኃላፊነት አለመወጣት ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 114553 /በቅጽ 20 እንደታተመ/ በሰጠው ውሳኔ በውል ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ በተካደ ጊዜ በመጀመሪያ ፊርማው በፎረንሲክ ምርመራ ዘዴ ሊረጋገጥ እንደሚገባና ፊርማው ሳይመረመር በምስክሮች ብቻ ተመስርቶ የሚሰጠው ውሳኔ ጠቅላላ የማስረጃ ምዘና መርሕን ያላገናዘበ ስለመሆኑ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል።

የጋብቻ ውሉ በሚች አቶ ታመነ መኮንን ተደርጓል ወይስ አልተደረገም የሚለው የፍሬ ነገር ጭብጥ ነው፤ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፤በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፤የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው።

ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ ከማስረዳት ደረጃ (standard of proof) አንጻር በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 172206 እና ሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው።

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪ የቀረበውን የጋብቻ ውል አመልካቾች የሚች አባታችን ፊርማ አይደለም በማለት ክደው ተከራክረዋል። ፊርማ በተካደ ጊዜ ፊርማው በፍ/ሕ/ቁ. 2008 አግባብ በፎረንሲክ ምርመራ ማጣራት ያስፈልጋል። የውል የፎረንሲክ ምርመራ ዉጤት እንደ ሙያ ምስክርነት ቃል (ቴክኒክ ምርመራ ዉጤት) ሲመዘን ከፍተኛ ዋጋ (high probative value) ተሰጥቶ እንደሚመዘን ከአጠቃላይ የማስረጃ መርህ የምንረዳው ነው። የውል ሰነድ ፊርማ ሲካድ በመጀመሪያ ፊርማውን በፎረንሲክ ምርመራ ማጣራት እንደሚገባና ፊርማው የማን ነው የሚለው በምርመራ ማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ውሉ ሲደረግ በነበሩ

እማኞችን በመስማት ማረጋገጥ እንደሚገባው ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 114553 ከሰጠው ውሳኔ መመልከት ይቻላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ወጪ ፊርማው እንዲመረመር ሳያደርጉ ምስክሮችን በመስማት ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ/ም የተደረገው የጋብቻ ውል መኖሩ ተረጋግጧል ሲሉ የደረሱበት መደምደሚያ የማስረጃ ምዘና መርሕን እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የተሰጠውን ትርጉም ያልተከተለ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 303616 ግንቦት 08 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 173973 ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ/ም ተጠሪን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ክፍል በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) ተሽሯል፡ ፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ/ም የተደረገውን የጋብቻ ውል ላይ ያለው ፊርማ ሟች አቶ ታመነ መኮንን መሆን አለመሆኑን በአመልካቾች ወጪ በፎረንሲክ ምርመራ በማጣራት ሟች ከተጠሪ ጋር በባሕላዊ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ጋብቻ የፈጸሙ ስለመሆን አለመሆኑ፣ በጋብቻ ውል ንብረቱ የጋራ መደረግ አለመደረጉና ተጠሪ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 1882 የሆነው ቤት ላይ ግማሽ ድርሻ መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑ ላይ አስቀድሞ ከተሰማው ማስረጃ ጋር በመመዘን በሕግ መሠረት እንዲወሰን ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- ውሳኔው ነሀሴ 06 ቀን 2016 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አረጋጋጭ ማስረጃነት አይውልም!